መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
አቅራቢዎች

# እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከሠራው በኋላ





ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus; Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): Bob Davies; Tammy S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት
ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው
ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ማንፈጠረን መጽሐፍ ቅዱስ ወይም
የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው የዞው
ዛር ከብዙ ዘመናት በፊት እንዲተፈጠረና
በመጀመሪያ የተፈጠረው ሰው አዳም
ተምሎ እንዳተሰየመ
ይናገራል።



እግዚአብሔር አዳምን ከምድር
አፈር አበጀው።



እግዚአብሔር የህይወትን እስትንፋስ በአዳም ውስጥ እፍ ባበት ጊዜ ህያው ሰው ሆነ።

እሱም ራሱን እጅግ በተዋበ ኤደን በሚበልበት ገነት ውስጥ አገኘው።



እግዚአብሔር አዳምን ከመፍጠሩ በፊት ምድርንና ሞላዋን በሙሉ እንደፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እግዚአብሔር ደረጃ በደረጃ ተራራዎችን፣ ሜዳዎችን፣ አበቦችን፣ ትላልቅ ...



... ዛፎችን፣ የሚያማምሩ አይን የሚስጡ ወፎችን (አእዋፍትን)፣ ንቦችን፣ በባህርና በየብስ ላይ የሚገኙትን በእግር የሚራመዱና በደረት የሚስቡትን እንስሳት ሁሉ ፈጠረ።



እግዚአብሄር ሁሉንም ነገር በሠማይና በምድር፣ በባህርም ሆነ በየብስ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ ፈጠረ ሁም ተፈጠሩ።



ከሁሉም ነገር በመጀመሪያ ወይም
እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር
ከመፈጠሩ በፊት ምንም
ዓይነት ነገር/ ፍጥረት
አልነበረም ነገር
ግን እግዚአብሔር
ብቻ ነበር። ምንም
ዓይነት ከፍታም ሆነ
ዝቅታ አልነበረም፤ ትናንት
ወይም ነገ በሚባል አልነበረም።



ምንም አይነት መጀመሪያ
የሌለው /ያነበረው
እግዚአብሔር
ብቻ ነው።
ከዚያም
እግዚአብሔር
አደረገው።





በመጀመሪያ
እግዚአብሔር ሠማይንና
ምድርን ፈጠረ።

መሬትም ቅርፅ አልባ
እና ባዶ ነበረች
ጨለማም
በጥልቁ
ውስጥ
ነበር።



እግዚአብሔር
“ብርሃን ይሁን
አለ” ብርሃንም
ሆነ።



ብርሃንም ሆነ። እግዚአብሔርም ብርሃን ቀን ብሎ ጨለማንም ምሽት ብሎ ጠራቸው። በመጀመሪያው ቀን ምሽትም ንጋትም ሆነ።



በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር በውሆች
መሃከል ጠፈር ይሁን ውሃና በውሃ መሃከል
ይካፈል አለ እግዚአብሔርም ጠፈርን አደረገ።



ሦስተኛውም ቀን እግዚአብሔር እንደህ አለ
“የብስም ይሁን” አለ እንደዳለውም ሆነ።



እግዚአብሔር ሣር፣ አበቦች ቁጥቋጦዎችና
ዛፎች እንዲሆኑ አዘዘ ሆኑም
እንዳቃሉ ተፈጠሩ።
ጧትም ማታም ሆነ

ሦስተኛው ቀን።

እግዚአብሔር ፀሐይና ጨረቃን ፈጠረ ማንም ሊቆጥራቸው የማይችላቸው ከዋኩብትም በሠማይ ላይ ፈጠራቸው። ከዚያም ጧትም ማታም ሆነ አራተኛው ቀን።



ቀጥሎም
እግዚአብሔር
የባህር ውስጥ
ፍጥረታትን፣
ዓሣዎችንና
ወፎችን
ፈጠረ።



በአምስተኛውም ቀን
እግዚአብሔር ህያው ነፉ
ያላቸውን በውሃ/በባህር
ውስጥ ያሉትን
የሚንቀሳቀሱትንም
ነገሮች ትልቁን ዓሣና
ትናንሽ ትላትሎችን፣
ረጃጅም እግሮች
የሏቸውን ሰጎኖች፣ እና
ትናንሽ ዲንቢጠችንም
በሙሉ በቃሉ ፈጠረ።



የውሃውን አካል
ክንዲሞሉት የተለያዩ
የዓሣ ዓይነቶችንና
በየብስና በባህር
በሰማይ ላይ
ክንዲበረሩ ውበት
የተላበሱ ወፎችን
ፈጠረ። አምስተኛው
ቀን ምሽትም
ንጋትም ሆነ።



ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገረ “ምድርም ህያው የሆኑ ፍጥረታትን ታምጣ የተለያዩ እንስሳት ልዩ ልዩ ተባዮች፤” እና በደረታቸው የሚሳቡ የምድር ፍጥረታት ሁሉ ተፈጠሩ ህያውም ሆኑ። ምድርን የሚያናወጡ ግዙፍ ዝሆኖች ጉማሬዎችና ሌሎም እንስሳት ተፈጠሩ።



አታላዮቹ ጦጣዎችና አስፈሪዎቹ አዞዎች፣ አስፈሪዎቹ ትላትሎች፣ ረዳጅሞቹ ቀጭኔዎች እና ሁሉም የእንስሳት ዓይነቶች በዚህ እለት በእግዚአብሔር ተፈጠሩ።

ንጋትም ምሽትም ሆነ አምስተኛው ቀን።



እግዚአብሔር ሌላም ተጨማሪ ነገር
በስድስተኛው ቀን ፈጥሯል። ይህም ፍጥረት
በጣ ልዩ ነው ለሠው ልጅ አሁን
ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው።
በየመልኩ የሚያፈልገው
የምግብ ዓይነትና
እዲያገለግሉት
እንሰሳት
ተፈጥረውለታል።



እግዚአብሔር እንዲህ አለ “ሰውን እንደመልካችን በምሳሌያችን እንፈጥ እሱም በምድር ላይ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ ይገዛ” ስለዚህ እግዚአብሔር ሰው በራሱ መልክ እንደምሳሌው ፈጠረው።



እግዚአብሔርም
አዳምን አለው
“ከኤደን ገነት
ውስጥ መብላት
የምትፈልገውን ሁሉ
ብላ ነገር ግን ክፉና
መልካምን ከምታሳዩህ
ዛፍ ፍሬን ፈጽሞ
እንዳትበላ አለው።



ከተከለከለው
ዛፍ ግን
ፍሬን ከበላህ
ትሞታለለህ
አለው።”



እግዚአብሔርም “ሰው ብቻው ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም ስለዚህ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት አለ።”



እግዚአብሔር ሁሉን አእዋፍትና አውሬዎችን ወደ አዳም አመጣቸው አዳም ለሁሉም ስም አወጣላቸው።ነገር ግን ከሁሉም ወፎችና አውሬዎች መሃከል የሚመቸው አንድም አልነበረም።



እግዚአብሔርም በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ
ጣለበት። ከሰውም አንድ የጎድን እንት



አወጣበትና ሴት አድርጎ
ካበጃት በኋላ ለአዳም
ሰጣት። የሠራትንም
ሴት የምትመች
ረዳት አድርጎ
ለአዳም ሰጠው።

እግዚአብሔርም በስድስት ቀናት ውስጥ ሁንም ነገር ፈጠረ። እግዚአብሔርም ሰባተተኛውን ቀን ቀድሶት የእረፍት ቀንም አደረገው።



በኤደን ገነት ውስጥ አዳምና ሔዋን
ፍጽም መልካምና ምቹ የሆነ ኑሮ
እግዚአብሔርን በመታዘዝ ይኖሩ
ነበር። እግዚአብሔርም ጌታቸው
ሆኖ የሚያዘጋጅና የቅርብ
ጓደኛቸው ነበር።



# እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከሠራው በኋላ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 1-2

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን
ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን
በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር
እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው
ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና
ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት
እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ
በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን
እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር
እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል።
እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ
ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16